የመጽሀፍ ትችት ፣

<u>ኃያሉ አሜሪካ ፣ የሙታን ማስታወሻ በኢ.ማኑዔል ቶድ</u>

በፈረንሳዩ የታሪክና የህዝብ ቁጥር ዕድገት(Demography) ተመራማሪ በኢ.ማኑዔል ቶድ(Emmanuele Todd) የተደረሰው መጽሀፍ ከሶቭየት ህብረት አገዛዝ መገርሰስ ወዲህ የቀረውና ብቸኛው ኃያል መንግስት የሚባለውን የአሜሪካንን የበላይነት መቦርቦርና ውድቀት የሚያሳይ የ252 ገጽ መጽሀፍ ነው

ኢ.ማኑዔል ቶድ በዚህ ግሩም መጽሀፉ የአሜሪካንን ኃያልነት መቦርበር ቀስ በቀስም እያለ በአንድ በኩል ተደማጭነት ማጣት ፣ በሌላ ወገን ደግሞ በተጨባጭ ኢኮኖሚ ፣ (Real Economy) በፖለቲካ ፣ በትምህርትና በዲፕሎማሲ ረገድ የበላይነቱን በጥምር የሚቀናቀኑ ኃይሎች ብቅ እያሉ እንደወጡ ፣ ይህም ሁኔታ ይህንን አትል የሚዘባነን ኃያል መንግስት እንዳስፈራውና በየቦታው እንደሚቅበዘበዝ ቁልጭ አድርጎ ያሳያል። የዛሬው የኃያሉ አሜሪካን መንግስት መገርሰስ በታሪክ እንደታየው የአቴኑንና የሮማውያኑን የመስፋፋትና የእብጠት ፖለቲካ ጋር እንደሚነፃፀር ፣ እንደዚህ ዐይነቱን የመስፋፋት ፖለቲካ የሚከተሉ የመጨረሻ መጨረሻ እጣቸው መውደቅና የታሪክ ትዝታ መሆኑን ኢ.ማኑዔል ቶድ በቲዎሪ ፣ በልምድና በአሀዝ በመደገፍ በሚገባ ያሳየናል ፣

እንደሌሎች ብዙ ጥናቶች ሁሉ ፣ ኢ.ማኑኤል ቶድ እንደሚያሳየው ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት መጨረሻ ጀምሮ እ.እ. እስከ 1965 ዓ.ም ድረስ አሜሪካን በሚሊታሪ ብቻ ሳይሆን ፣ በኢኮኖሚም ሆነ በፖለቲካ እንዲሁም በርዕዮተዓለም የበላይነትን እንደተቀዳጀና በዓለም አቀፍ ደረጃም ተቀባይነት እንደነበረው ነው። አሜሪካ በሁለተኛው ዓለም ጦርነት ማግስት የበላይነትን ሊቀዳጅ የቻለው ከዚያ ቀደም ብሎ ወደ ውስጥ ያተኮረ እርስ በርሱ የተሳሰረ የኢንዱስትሪ ፖለቲካና የህብረተሰብ ግንባታ ማካሄድ በመቻሉ ነው። በጦርነት ባለመካፈሉም ኃይሉና ሀብቱ ሊወድም አልቻለም። ይህ ሁኔታም እስትንፋስ ስለሰጠው በሁሉም አቅጣጫ የበላይነትን ሊቀዳጅ ችሏል። እስከ ሁለተኛው ዓለም ጦርነት ድረስ የባላይነትን ይዛ የቆየችው እንግሊዝና ሌሎች የኢንዱስትሪ አገሮች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ሂትለር በቆሰቆሰው ጦርነት በመካፈላቸውና በመመታታቸው ከጦርነቱ በኋላ በሚሊታሪ ፣ በኢኮኖሚና በፖለቲካ ተዳክመው እንደነበር የታወቀ ነው። ስለሆነም አዲስ የተፈጠረውን የዓለም አቀፍ ሁኔታ በመጠቀም አዲስ ኢንስቲቱሽኖችን በመመስረትና ተጽዕኖውን በማሳደር አሜሪካን የመሪነትን ደረጃ ይዞ እንደነበርና በየቦታውም ርዕዮተዓለማዊ ፣ ኢኮኖሚያዊ ፣ ፖለቲካዊና የሚሊታሪ ተጽዕኖ ማሳደር ችሎ እንደነበር ግልጽ ነው።

ለአሜሪካ የበላይነት መቀዳጀት ከላይ የተጠቀሱት ብቻ በቂ አልዳነበሩ ኢ.ማኑዔል በዝርዝር ያሰቀምጣል። አሜሪካን በአዳም ስሚዝና በሪካርዶ የረቀቀውን ዓለም አቀፋዊ የን ግድና የስራ ክፍፍል ቲዎሪ ቀጥታ በመውሰድና በማስፋፋት እንዲሁም መመሪያው በማድረግ ብዙ አገሮች በዚህ ርዕዮተ ዓለም እንዲጠመዱ በማድረግ የዓለም አቀፍን የኢኮኖሚ ሁኔታ አረማመድና አቅጣጫ ማሲያዝ ችሏል። በቲዎሪው መሰረት በንግድና በስራ ክፍፍል የሚሳተፉ አገሮች እንደ ምጣኔ ሀብት ይዘታቸውና በዓለም አቀፍ ገበያ ላይ እንደሚኖረው የምርት ጥያቄ ያላቸውን ውስን ካፒታል በዚሁ መስክ ካዋሉና ከሰለጠኑ ከወጭ ካፒታልና „ዕውቀት" ወደ ውስጥ በማስገባት ቀስ በቀስ ግን ደግሞ በርግጠኝነት አጠቃላይ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ይጎናጸፋሉ የሚል ነው። በሞላ ጎደል ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት በኋላ ፣ በተለይም በኮሪያ ጦርነት ሰሞን በዓለም ገበያ ላይ የጥሬ ሀብትም ሆነ የኢንዱስትሪ ምርት ንግድ የጦፈበት ዘመን እንደነበር ሁኔታውን የተከታተለ ሊገነዘበው ይችላል። አሜሪካን ይህንን አስታኮ በተለይም በሶስተኛው ዓለም አገሮች የትምህርት ተቅዋማትና ልዩ ልዩ ኢንስቲቱሽኖች

ውስጥ ቀስ በቀስ ሰርጎ በመግባትና  የራሱን ሰዎች በመመልመል በተለይም በተወሰነው የህብረተሰብ ክፍል የርዕዮተዓለምና የባህል ድል ሊቀዳጅ ችሏል። በየአገሩ ዕድሉን ከአሜሪካን የፖለቲካና የኢኮኖሚ ዓለም አቀፋዊ  እንቅስቃሴ ጋር ያዛመደ ልዩ የህብረተሰብ ክፍል ብቅ ማለት ቻለ። ይህ ሁኔታ አሜሪካን በየቦታው ገብቶ እንዲፈተፍትና የብዙ ሚለዮንን ህዝቦች ዕድል ሊወስንና የየአገሮችን ብሄራዊ ነፃነት እንዲቀናቀን በር ከፍቶ ሰጠው። መዝናናትና ዓለምን እንደፈለግሁ መበወዝ እችላለሁ በሚል ፣ የዓለም አቀፍን ህግ በመጣስ አገሮችንም እሰስከመውረርና የሚቀናቀነውን እሰከማጥፋት ደረሰ።

ከዚህ ባሻገር በሁለተኛው ዓለም ጦርነት ኢኮኖሚያቸው የተከሰከሰውን የምዕራብ አውሮፓና የጃፓንን ኢኮኖሚ ተመልሶ እንዲገነባ በማገዝ ፣  በሁሉም አቅጣጫ ሀብት እን ዲንቀሳቀስ ሲያደረግ ፣ በሌላ ወገን ደግሞ በተለይም የጀርመንና የጃፓን ኢኮኖሚ እንዲን ሰራራ በማገዝ ሳያውቀው የሚቀናቀናቱን ኃይሎች ሊያዘጋጅ ቻለ። ተወዳዳሪ አጋጠመው ማለት ነው። እንደ ኢማኑዌል አተናተን ከ1965 ዓ.ም ጀምሮ በተለይም የሪየል ኢኮኖሚ እንዲያም ሲል የውጭው ንግድ ለአሜሪካን አመቺ ባልሆነ ሁኔታ እየተዛባ ይመጣል። ይህንን በዝርዝር ከማየታችን በፊት ፣ ኢማኑዌል  የአሜሪካን የበላይነት በሁሉም አቅጣጫ እንዴት እንደተቦረቦ የሚመረኮዝበትን ቲዎሪ በዝርዝር እንመልከት።

ኢማኑዌል በመጀመሪያ የሚነሳው ባለፉት አስር ዓመታት በምዕራቡ የዜና ማሰራጫዎች በየቀኑ የሚቀርቡልን በየቦታው የተካሄዱትና የሚካሄዱት የእርስ በርስ ጭፍጨፋዎች ፣ የሀይማኖት ግጭቶች... ወዘተ ፣ ዓለም እንዳለቀለትና የሰው ልጅም ከመሻሻል ይልቅ የኋሊት ጉዞ ማድረግ እንደጀመረ ነው ሲያሳዩን የከረሙት። ለዚህ እርስ በርስ መተላለቅ፣ የሀይማኖት ግጭት፣ የቴሮሪዝም መስፋፋት ዋና ው ምክንያት በግሎባላይዜሽን ስም የተካሄደውና የሚደረገው ኢኮኖሚያዊና የፊናንስ መስፋፋት ያስከተለው በደሀና በሀብታም አገሮች የተፈጠረው የዕድገት መዛባት ነው። በተለይም በነፃ ንግድ ስም የተካሄደው ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ በሀገሮች መሀከልና እን ዲሁም በአንድ አገር ውስጥ ጤናማ ያልሆነ ውድድር በመፍጠር  ጥቂቶች ሀብታም እየሆኑ ሲመጡ ሰፊው ህዝብ ደግሞ ወደድህነት እየተገፈተረ መጣ። በተለያዩ መንገዶች ሀብት ከደሀ አገሮች ወደ ኢንዱስትሪ አገሮች በመፍሰስ የኢኮኖሚ ዕድገት መዛባትና ህብረተሰብአዊ ግኑኝነት መዘበራረቅ ዐይነተኛ መለያ ሆኑ። ይሁንና ይህ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት መዘባት ቢኖርም በብዙ አገሮች የባህል አብዮት ማካሄድ ፣ እንደተፈራው ሳይሆን የህዝብ ቁጥር መቀነስና  የህዝቦች እርስ በርስ መጋባት የዲሞግራፊ ለውጥ በማምጣት ለአሜሪካን የበላይነት መገርሰስ ከፍተኛ አስተወፅዎ አድርጋል። እንዴት?

ኢማኑዌል በአሃዝ ለማመልከት እንደሚሞክረው ከ1980-200 ድረስ በተለያየዩ አገሮች የመጻፍና የማንበብ እንዲያም ሲል የአኗኗር ስልቶች በመለወጥ በሰው አስተሳሰብ የተሻለ አመለካከት ፈጥሯል። እንደሚታወቀው አንድ ህዝብ መጻፍና ማንበብ እንዲሁም ሂሳብ ሲችል በተፈጥሮ ላይ ያለው ቁጥጥር እየጨመረ ይመጣል። በኤሲያና በሩቅ ምስራቅ የሚታየው የኢኮኖሚ  ዕድገት የዚህ የሰው ልጅ የማሰብ ኃይል ዕድገት ከፍ እያለ መምጣት ነው። ይህ የመጻፍና የማንበብ ሁኔታ በብዙ አገሮች መስፋፋት ከሞላ ጎደል በአውሮፓ ውስጥ በ17ኛውና በ18ኛው ዐመተ ምህረት ይካሄድ የነበረውን የባህል እንቅስቃሴ ዐይነት ይመስላል። ይሁንና ግን ይላል ኢማኑዌል ፣ ይህ የመጻፍና የማንበብ መስፋፋት በአለፉት ዐመታት በግሎባላይዜሽንና በነፃ ንግድ የተነሳ ሊገታ ችሏል ይላል። ይህም ሆኖ በአጣቃላይ የግሎባላይዜሽንን እንቅስቃሴ ስንመለከት ብዙ የመልቲ ናሽናል ኩባንያዎች ኢን ዱስትሪዎቻቸውን ወደ ላቲን አሜሪካና ወደ አሽያ እየወሰዱ የሚተክሉት በሰራተኞች የመጻፍና የማንበብ ችሎታ የተነሳ ነው። በዚህም የተነሳ እነዚህ ዓለም አቀፋዊ ኩባንያዎች ከፍተኛ ትርፍ ማካበትና ወደ ኢንዱስትሪ አገሮች ማስተላለፍ ችለዋል። ይህ ዐይነቱ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ በየአገሮች ውስጥ ያልተስተካከለ ዕድገት በመፍጠሩ የተወሰነው

***የህብረተሰብ ክፍል የተሻለ ኑሮ አገኛለሁ በማለት ወደኢንዱስትሪ አገሮች እንዲፈልስ አድርጓል። በሌላ አነጋገር ይህ የህዝብ መፍለስ በሶስተኛው ዓለም አገሮች ውስጥ የመንፈስ ድህነትን ወይም የተማረ ሰው እጥረትን አስከትሏል።***

***በየአገሮች የመጻፍና የማንበብ መስፋፋት ፣ የዕውቀት ጥልቀትና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ጋር ተደምሮ በዚያውም መጠንም የህዝብ ቁጥር እየቀነሰ መጥቷል።ድሮ በህዝብ ብዛት በመቶ ሲለካ በየዐመቱ ከፍተኛ ቁጥር ያሳዩ የነበሩ እንደቻይና የመሳሰሉ አገሮች የህዝቦቻቸውን ቁጥር መጨመር መግታት ችለዋል። ይህ የህዝብ ቁጥር ዕድገት መቀነስ አሁንም ሀይማኖት በጥብቅ በተያዘበት በአንዳንድ የአረብ አገሮች ገና ፍሬ ባያሳይም ይህ ሁኔታ ሊለወጥ እንደሚችል ያመለክታል። ለምሳሌ ቱርክና ኢራን የዲሞግራፊ ዕድገታቸውን መግታት እንደቻሉና በአንዳንድ የድሮ የሶቭየት ሪፑብሊክ አገሮችም አዝማሚያው ጥሩ እን ደሆነ ኢማኑዌል በትንተናው ያሳየናል።***

***የትምህርት መስፋፋት ፣ የሰዎች የማሰብ ኃይል መዳበርና የህዝብ ቁጥር መቀነስ በየአገሮች ውስጥ ግለሰብአዊና የሊበራል ዲሞክራቲ አስተሳሰብ እንዲዳብር ሀኗል ይላል ኢማኑዌል። በዚህም የተነሳ አንድ ቀን የዐለም ሀዝብ የበለጠ የመግባባትና ጦርነትን የመቀነስ ኃይሉ እየጨመረ ይመጣል። ኢማኑዌል እንደሚለን ዛሬ በዐለም አቀፍ ደረጃ የሚታየው ንቃተ-ህሊና ፉኩማያ እንደሚለን የግዴታ ከማቴሪያላዊ ሁኔታ መለወጥ ጋር የተያያዘ ሳይሆን በመጀመሪያ የትምህርት መስፋፋትና የሰዎች የጭንቅላት መዳበር ጋር በጥብቅ የተያያዘ ነው ይላል። በዚህ አኳያ በግሎባላይዜሽን አማካይነት በየአገሮች ውስጥ የተፈጠረው የሀብት ክፍፍል መዛባት እስከተወሰነ ደረጃ በዕውቀት መስፋፋት ሊካካስ ችሏል። ይሁንና አገሮች ከጥንታዊ የአኗኗር ዘዴ ወደ ዘመናዊነት ሲሸጋገሩ በስልጣኔው ውሰጣዊ ኃይል ደካማነት በሚፈጠረው ዝብርቅርቅ ሁኔታ የተነሳ ብዙ የሶሰተኛው ዐለም አገሮች የርዕዮተ ዓለም ውዥንብር ውስጥ ይገባሉ። ዛሬ በየቦታው የምናየው የሀይማኖት አክራሪነት ከዚህ ጋር በጥብቅ የተያያዘ መሆኑን ኢማኑኤል ያስረዳል። ይህ ሁኔታ ጊዚያዊ እንደሆነና በንቃተ-ህሊና ማደግና በተስተካከለ የኢኮኖሚ ዕድገት ሊወገድ እንደሚችል ከኢማኑዌል ጽሁፍ መረዳት እንችላለን።***

***ወደ ዋናው መሰረተ-ሃሳብ ለመግባት ኢማኑዌል የአሜሪካንን የውስጥ መቦርቦርና የማይቀረውን የበላይነት ማጣት በታሪክ ውስጥ እንደታየው ከጥንቱ የሮምና የአቴን አገዛዝ ጋር በማነፃፀር እጅግ በጣም ጥሩ ትምህርት ይሰጠናል። ኢማኑዌል እንደሚተነትነው የሮምና የአቴን አገዛዝና መስፋፋት የተለያየ ባህርይና አረማመድ እንደነበረው ነው። በመጀመሪያ አቴን የፐርሺያኖችን ወረራ መክቶ ለመመለስ ከስፓርታና ከሌሎች አካባቢው አገሮች ጋር ስምምነት ትመሰርታለች። የፐርሺያ ወራሪ ጦር ከተደመሰሰ በኋላ በመጀመሪያው ወቅት ይታይ የነበረው የአቴኑ ዲሞክራሲያዊና የፌዴራል አገዛዝ ሌሎች ተቀጥያ ግዛቶችን መብታቸውን እየገፈፈና የግዴታ ህበት ወደ አቴኑ አገዛዝ እንዲያስተላልፉ በማድረግ በእኩልነት ላይ የተመሰረተው ፌዴራላዊ አገዛዝ ሊፈርስ ችሏል። ይህ ሁኔታ የኋላ ኋላ ስፓርታን በአቴን ላይ በማስነሳት የአቴን የበላይና የመስፋፋት አገዛዝ ሊገረሰስ ችሏል። የሮማውያን አገዛዝ ከመጀመሪያውኑ እንደአቴኑ የበላይነት አገዛዝ በስምምነት ላይ የተመሰረተ ሳይሆን ቀጥተኛ ወራሪነትና አገሮችን ተበዝባዥ ማድረግ ነው። ይሁንና የሮማውያኑ አገዛዝ በሄደበት ቦታ ሁሉ መንገዶችን በመስራት ፣ ከተማዎችን በመገንባት አገዛዙንም ለማጠንከር ይጥር እንደነበር የኢማኑዌል ጽሁፍም ሆነ ታሪክን ላገላበጠ ሊገነዘበው ይችላል። ይሁንና ይህ አገዝዝ ይበልጥ ብዝበዛንና የኋላ ኋላ በአገዛዙ ዘንድ መባለግንና የበለጠ ማበጥን በማስከተሉ የበላይነቱ እየተገረሰሰና የመጨረሻ መጨረሻ ወደ ውድቀት እንዳመራ ማየት እንችላለን። በተለይም የሮም አገዛዝ ወደ ውጭ የበለጠ እየተስፋፋ ሲሄድ ወደውስጥ መደረግ ያለበትን ዕድገት እየረሳ ይመጣል። በሀብታምና በደሀ መሀከል ያለው ልዩነት ይሰፋል። ኢማኑዌል የአርሰቲቶልስን ግሩም አስተያየት በመጥቀስ በሁለቱም አገዛዝ ዘንድ በመሀከሉ ጠንካራ ከበርቴያዊ መደብ ባለመፈጠሩ ለሁለቱም አገዛዝ***

ውድቀት ምክንያት መሆኑ የማይታበል ሀቅ መሆኑን ቁልጭ አድረጎ ያሳየናል። ይህ ሁኔታ ዛሬ በብዙ የሶስስተኛው ዐለም አገሮች የምናየውን ከበርቴያዊ አልባ አገዛዝና የጥቂቶችን የስልጣን መባለግ ሁኔታ ያመለክተናል።

ኢማኑዔል ይህንን መሰረት በማድረግ በተለይም የዛሬው ዐለም ሁኔታና አረማመድ ይመለከተናል የሚሉ ሰዎች ሊቀስሙት የሚችሉት ትምህርት እንዳለ ይጠቁመናል። ለዛሬው በዐለም አቀፍ ደረጃ የሚካሄደው ግሎባላይዜሽን ዋናው ምንጩ አሜሪካን እንደሆነና የሚመራበትም ርዕየተ-ዓለም በአንድ በኩል በአንድ አገር ውስጥ ሀበት በተስተካከለ መልክ እንዳይከፋፈል የሚያደርግና መንግስታትን የበለጠ በሀብታሞች ቁጥጥር ስር እንዲወድቅ የሚያደርግ ፣ በሌላ ወገን ደግሞ በአገሮች መሀከል የዕድገት ልዩነት እንዲኖር ያደረግና የሚያደርግ በነፃ ገበያና ንግድ የሚካሄድ አደገኛ ፍልስፍና እንደሆነ ያመለክተናል። ይህ በአሜሪካን አገር የዳበረው የነፃ ንግድ ፍልስፍና የመጨረሻ መጨረሻ የዐለምን ህዝብ ማድኸየቱና ማዘበራረቁ ብቻ ሳይሆን እራሱን አሜሪካንን ከአምራችነት ወደ ተጠቃሚነት እን ደገፈተረው ፣ ሌሎች አገሮች በአሜሪካን ላይ ጥገኛ ሳይሆኑ እራሱ አሜሪካን በሌሎች አገሮች ላይ የበለጠ ጥገኛ እየሆነ እንደመጣና ውስጣዊ የተጨባጭ ኢኮኖሚ መሰረቱ እን ደተቦረቦረ ከኢማኑዔል ጽሁፍ መረዳት እንችላለን። ይህ የአሜሪካን የውስጥ ተጨባች ኢኮኖሚ ዘርፍ መቦርቦር ሌላው የዐለም ሀዝብን አምራችና አሜሪካንን ደግሞ ንጹህ ተጠቃሚ አድርጎታል። በዚህም የተነሳ ፣ የአሜሪካን የውጭ ንግድ ሚዛን ከብዙ አገሮች ጋር የተዛባ ነው። ለምሳሌ ይህንን የንግድ ሚዛን መዛባት በአሀዝ ስንመለከተው ፣ አሜሪካን ከቻይና ጋር በ2001 ዓ.ም ብቻ የ83 ቢለዮን ዶላር ፣ ከጃፓን ጋር የ68 ቢሊዮን ዶላር ፣ ከአውሮፓ የጋራ ገበያ አገሮች ጋር የ60 ቢሊዮን ዶላር ፣ ከደቡብ ኮርያ ጋር የ13 ቢሊዮን ዶላር እንዲሁም ከራሽያና ከሌሎች የድሮው የሶቭየት ሬፑብሊክ አገሮች ጋር በጠቅላለው ወደ 10 ቢሊዮን ዶላር የሚደርስ የንግድ ሚዛን መዛባት አለበት። በጠቅላላው የአሜሪካን የውጭ ንግድ ሚዛን ከላይ በተጠቀሰው ዓ.ም ብቻ 450 ቢሎዮን ዶላር ተዛብቶበታል። በሌላ አነጋገር ወደ ውጭ ከሚያሰወጣው የኢንዱስትሪና የእርሻ ምርት ውጤት ወደ ውስጥ የሚያሰገባው ይበልጣል። ይህ የንግድ ሚዛን መዛባት አሜሪካን የጥሬ ሀብት ብቻ በማስገባቱ የመነጨ ሳይሆን ንጹህ የኢንዱስትሪ ምርት ውጤት ነው። በዚህም የተነሳ ይህንን የተዛባ የን ግድ ሚዛን ለማጣጣት ከውጭ ካፒታል በቀን 1. 2 ቢሊዮን ዶላር የሚጠጋ ማስገባት አለበት ማለት ነው። ይህ በራሱ ደግሞ ዕዳውን ሲያከማችበት በዚያው መጠንም ወለድ ከፋይ በመሆን የዙሪያ ጥምጥም ውሰጥ ወድቆ እንደሚገኝ እንገነዘባለን። በዚህ ሁኔታ አሜሪካን የሁለተኛው ዐለም ጦርነት አካባቢና በኋላም የነበረውን በኢንዱስትሪ ምርት ዕድገት ቅድሚያ በአውሮፓ የጋራ ገበያ አገሮችና በጃፓን እንዲነጠቅ አድርጎታል።

ይህ በእንደዚህ እንዳለ ፣ በተይለይም የአንዳንድ ትላልቅ ኩባንያዎች ከአምራችነት ወደ ቁማር ጨወታ(Stock Market) ማምራት በተለይም በውሀ ክፍፍልና በሀይል ስርጭት ያለውን ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ያናጋዋል። ከዚህ ጋር በመያያዝ ከትምህርት እስከ ጤና መስክና ሌሎችንም ለሰፊው ህብረተሰብ የሚጠቅሙ የአገልግሎት መስጫ መስኮች በኒዎ ሊበራል ርዕዮተ-ዐለም አስተሳሰብ ስለወደቁና መመሪያቸውም ይህ በመሆኑ የጠቅላላው ህበረተሰብ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ኃይል ይናጋል። በተለይም በፕሬዚደንት ክሊንተን የስምን ት ዐመት አገዛዝ ኢኮኖሚው ያደገ ቢመስልም ይህ ኢኮኖሚያዊ ዕደገት ኢማኑዔል ብቻ ሳይሆን ሌሎችም እንዳመለከቱት አብዛኛው የስታትስቲክ ሸወዳ እንደነበር ሀቁን መገንዘብ ይቻላል። ለምሳሌ ብዙ የኮምፒዩተር ቺፖች አሜሪካን አገር ሳይሆን ቻይናና ሌሎች የሩቅ ምስራቅ አገሮች ነው የሚመረቱት። እነዚህ የኮምፐዩተር ትናንሽ ክፍሎች አሜሪካን ከመጡ በኋላ ተገጣጥመው ልክ ጠቅላላው ምርት እዚያው እንደተመረተ ሆኖ በጠቅላላው ዐመታዊ የምርት ክንውን ስሌት ውስት ይገባል። ይህ የማጭበርበር ሁኔታ የግዴታ ኢኮኖሚው እን ዳደገ ሆኖ ይቀርባል። ይህንንም ለመገንዘብ በትላልቅ የኢኮኖሚ ተቆጣጣሪዎች ይካሄድ የነበረውን ውንብድናና ወደ ውጭ በይፋ የወጣውን የቢላንዝ መዛባት ሁኔታ የተመለከተ ኢኮኖሚው እንደተነገረው በክሊንተን ዘመን በተጨባጭ እንዳላደገ መመልከት ይቻላል።

ይህ በኒዎ ሊበራሊዝም ላይ የተደገፈ የኢኮኖሚ ፖሊስ የግዴታ ወደ ውስጥ ልክ እንደ ሮማውያን አገዛዝ ዘመን ልዩ ዐይነት የኦሊጋርኪ መደብ ብቅ ብሎ እንዲወጣ አድርጓል። አዲሰና ታሪከ-ቢስ የኦሊጋርኪ መደብ በመፈጠሩም፣ በኢማኑዌል አተናተን በህብረተሰቡ ውስጥ ልዩ ዐይነት የሀብት ሽግሽግ ተፈጥሯል። ጠበቃዎች ፣ በፊናንሰ መስክ ውስጥው ተቀጥረው የሚሰሩና ከዚህ መስክ ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የተሳሰሩ ግለሰቦችና ኩባን ያዎች የዚህ የአዲሱ ኦሊጋርኪ መደብ ሀብት ተካፋይ ናቸው። አብዛኛው ገንዘብ በአክሲዮን ገበያ ላይ የሚሽከረከርና ለፍጆታ የሚውል ነው። በሌላ ወገን ግን የአብዛኛው ህዝብ ገቢ እየቀነሰ በመምጣቱ፣ በአንድ በኩል ሁለትና ሶስት ስራ እየሰራ እንዲኖር የተገደደው ቁጥር እየጨመረ መጥቷል ፣ በሌላ በኩል በቁጠባ መልክ ባንክ ውስጥ የሚቀመጠው ገንዘብ ኔ ጋቲቭ ነው። አብዛኛው የአሜሪካን ህዝብ በዕዳ ተተብትቦ የተያዘ በመሆኑ በኑሮው እርግጥኛ አይደለም። በተጨባጭ የኢኮኖሚ መስክ መዳከም ፣ በሰፊው ህዝብ ገቢ መቀነስ ፣ በኩባን ያዎች የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ መቀዝቀዝና የመንግስቱ ገቢ መቀነስ የጠቅላላውን ፣ ማለትም የህዝቡን ፣የኩባንያዊችንና የመንግሰትን ዕዳ ወደ ላይ እንዲተኮስ አድርጎታል። በአሁኑ ወቅት ጠቅላላው ዕዳ 32 ሺህ በሊዮን ዶላር እንደሚጠጋ ስታትሰቲክስ ያሳያል። ይህ በእንደዚህ እንዳለ በፊናንስ ገበያ ላይ የሚሽከረከረው ገንዘብ በታሪክ ውስጥ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ እንዲያድግ አድርጎታል። ይህ የሀብት በጥቂት ግለሰቦች እጅ መከማቸት ፣ ወደተወሰነው የህብረተሰብ ክፍፍል መሸጋሸግና ፣ በሌላ ወገን ደገሞ አብዛኛው ህዝብ ወደ ድህነት መገፋተር በጠቅላላው የግለሰብአዊነት ስሜት እንዲጠነክርና ህብረተሰብአዊ ሃላፊነት እንዲዳከም አድርጓል።

ይህንን የሀብት ክፍፍል በአሀዝ ስንመለከተው ፣ 5% የሚሆነው የህብረተሰብ ክፍል በ1980 ዓ.ም በጠቅላላው የህዝብ ገቢ ውስጥ 15.5% ይይዝ የነበረው በ2000 ዓ.ም ይህ ገቢ ወደ 21.9% አድጓል። በዚህ ጊዜ ውስጥ ሀብታም ከሚባለው 20% የህብረተሰብ ክፍል ውስጥ ገቢው ከ43.1% ወደ 49.4% አድጓል። በሌላ በኩል ደግሞ 80% የሚሆነው ህዝብ ዐመታዊ ገቢ ከ56.9% ወደ 50.6% ዝቅ ብሏል። የመጨረሻ ደሀ የሚባለው የህብረተሰብ ክፍል ደግሞ ከ24.7 በመቶ ወደ 22.9 በመቶ ፣ ከ17.1 በመቶ ወደ 14.9 በመቶ ፣ ከ10.6 በመቶ ወደ ወደ 9.0 በመቶና ከ4.5 በመቶ ወደ 3.7 በመቶ ዝቅ ብሏል። በአንድ መጽሄት በተደረገ ጥናት በጣም ሀብታም የሚባሉት 400 ሰዎች ከአስር ዐመት በኋላ ሀብታቸው በአስር እጅ ሲያድግ ፣ በዚህ ጊዜ ውስጥ ጠቅላላው የኢኮኖሚ ዕድገት በእጥፍ ብቻ ማድግ ችሏል። በኢማኑዌል አተናተን ይህ የሀብት ክምችትና ስግሽግ ብሄራዊ ብቻ ሳይሆን ዐለም አቀፋዊ ተጽዕኖም አለው። የአሜሪካ የዛሬው ሀብት ክምችት ወደ ውስጥ አብዛኛውን ህዝብ የሚያደኽይ ብቻ ሳይሆን ፣ በተለያዩ መሳሪያዎች ከሌሎች አገሮች ሀብት በመምጠጥ አገራዊና ዐለምአቀፋዊ መዛባትን በማስከተል እርስ በርሱ የተሳሰረ ሰፊ ህዝብን የሚጠቅም ኢኮኖሚያዊ ዕድገት እንዳይመጣ እንቅፋት ሆኗል። በዚህም የተነሳ የዛሬው የአሜሪካን የመንግስት መኪና የግዴታ በጣም ሀብታም ከሚባሉት ጋር በጥብቅ የተሳሰረና በቀጥታ የነሱን ጥቅም የሚያስጠብቅ በዐለም አቀፍ ደረጃ እጅግ አደገኛ ኃይል ሆኖ ወጥቷል።

የአሜሪካ የበላይነት መሸርሸር ኢኮኖሚያዊ ብቻ ሳይሆን የህዝቡን የእርስ በርስ ግኑኝነት ለተመለከተ ጠቅላላው ህብረተሰብ ወደፊት ሊናጋ እንደሚችል መረዳቱ ከባድ አይሆንም። የአሜሪካን መንግስትና በተለይም የላይኛው የህብረተሰብ ክፍል የሚከተሉት ፖለቲካ አንዱን የሚያርቅ ሌላውን ደግሞ የሚያሰጠጋ እጅግ አደገኛ ህብረተሰብአዊ ፖሊሲ ነው። በአሜሪካን የኢኮኖሚና የፖለቲካ ክንዋኔ ውስጥ የይሁዲዎችና ከእሺያ የመጡ ሰዎች እያደገ ሲመጣ ፣ ጥቁሮችና የላቲን አሜሪካ ህዝቦች ግን የማደግ ዕድላቸው በተለያየ መን ገድ የተዘጋ ነው። የእርስ በርስ መጋባትንና ጎረቤት ሆነ የመኖርን ሁኔታ ስንመለከት ፣ ከጥቁሩ ዜጋ ጋር ተጋብቶ የሚኖረው ነጭ ቁጥር እዚህ ግባ የሚባል አይደለም። እንደዚሁ ጥቁሩ ህዝብ ከነጩ ተገልሎ የሚኖርና በራሱ ላይ ዕምነት እንዳይኖረው ልዩ ልዩ ሻጥሮች የሚሰሩበት ነው። በሌላ ወገን ግን ይሁዲዎችና ከአሺያ የመጡ ለጋብቻም ሆነ አብሮ

ለመኖር ይመረጣሉ። ይህ ዘረኛ የአሜሪካን መንግስት ፖሊሲ በዚህ ላይ ብቻ የሚቆም አይደለም። ምንም ወንጀል ሳይሰራ በየእስርቤቱ የሚወረወረው የስፓኒሽ ደም ያለው ዜጋና የጥቁሩ ህዝብ ቁጥር እየጨመረ መጥቷል። በዚያው መጠንም ካለበቂ ማስረጃ የሞት ፍርድ የሚፈረድበት ጥቁር ቁጥሩ በከፍተኛ ደረጃ ጨምሯል። ይህ ሁኔታ የአሜሪካንን ግዙፍነት የሚያረጋግጥ ሳይሆን ውስጣዊ ድክመቱን የሚያመለክትና ጠቅላላው ህብረተሰብ በተዛባ የኦሊጋርኪ የኢኮኖሚ አወቃቀር ፣ የህብረተሰብ ፖሊሲና የተዛባ ህግና የፍርድ አሰጣጥ ላይ የተገነባ መሆኑን ነው።

ውስጣዊ የኢኮኖሚና ህብረተሰብአዊ መዛባት በዚህ መልክ ሲዋቀር ፣ ለሚሊታሪ የሚወጣው ወጭና መንግስቱም ከጦር መሳሪያ አምራች ኢንዱስትሪ ጋር ያለው ግኑኝነት እየጠነከረ መጥቷል። የአሜሪካን መንግስት ለመከላከያ የሚያወጣው ወጪ በዐለም ላይ ከሚወጣው ጠቅላላ የመከላከያ ባጀት አንድ ሶስተኛውን ይይዛል። አሜሪካ በከፍተኛ ቴክኖሎጂ የተዋቀረ የመከላከያ ኃይል ቢኖረውም እስካሁን ድረስ በጦር ሜዳ ላይ የገጠመው ከደካማዎች ጋር በመሆኑ የተፈተነ አይደለም። የቬትናም ጦርነት እንዳረጋገጠው አሜሪካን በምድር ጦር ጥንካሬ ሊታማ የሚችል ኃይል አይደለም። ዋናው ድክመቱም እዚህ ላይ ነው። ይህ ዐይነቱ የሚሊታሪና የኢንዱስትሪ ውስብስብ ግኑኝነት ሀብትን ከሌላው የኢኮኖሚና የማህበራዊ ዘርፎች በመምጠጥ አብዛኛውን ህዝብ ወደ ድህነት እን ደሚገፈትረውና በመንግስቱና በህዝቡ መሀከል ያለው ቅራኔ እየሰፋ እንደሚሄድ በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል።

በኢማኑዌል አተናተን ዛሬ አሜሪካን በየቦታው ጣልቃ መግባትና መንደፋደፍ ድክመቱን የሚያመለከት ነው። በአሁኑ ወቅት የበላይነቱን የሚቀናቀኑ በጋራም ሆነ በተናጠል የሚጋፉት ኃይሎች ብቅ ማለት እንደጀመሩ ያሳየናል። በአንድ ወቅት ወደ መንኮታኮት የደረሰው ሶቭ የት ህብረት ፣ ከዚያ መፈራረስ የወጣው የራሺያ መንግስት ቀስ በቀሰ ግን ደግሞ በእርግጠኝነት ኢኮኖሚውን እያሳደገና ቴክኖሎጂውን እየገነባ ነው። የቻይና ኢኮኖሚ ማደግና ዐለምአቀፋዊ ተቀባይነት ማግኘት ፣ የአውሮፓ የጋራ ገበያ ጥንካሬና ፖለቲካዊ ትርጉም አሜሪካን እንደፈለገው እንዳይፈነጭ ወደ ማገድ ደርሷል። በኢማኑዌል ዕምነት ወደ ፊት የዐለም መዲናዎችና ዐለም አቀፋዊ ትርጉም የሚኖርባቸው ቦታዎች ኦይሮ አሺያ የሚባለው በአውሮፓና በድሮ የሶቭየት ሪፑብሊክ አካባቢ የሚገኙ አገሮች ነው ይለናል። ለዚህም የአውሮፓ መንግስታት ከራሽያ ጋር በመተማመንና በመከባበር የጋራ የኢኮኖሚ ትስስርና የጠነከረ ፖለቲካ ግኑኝነት ማካሄድ እንዳለባቸው ይጠቁመናል። አሜሪካን ፣ ይህ ከውስጥና ከውጭ የደረሰበትን ኢኮኖሚያዊም ሆነ ፖለቲካዊ ድከመት ለማዘናጋት ሲል ደካማ አገሮችን በማሰስና የማይሆን ስም በመስጠት ወደ ቀትር እባብነት እንደተለወጠ ኢማኑዌል ያስረዳናል። ስለዚህም በአንድ በኩል በቴሮሪዝም ስም እያሳበበ ፣ በሌላ በኩል ደግሞ በሰሜን ኮርያ ፣ በኢራክና በኢራን ላይ አደገኛ ኃይሎች ናቸው በሚል የሚያካሄደው ዘመቻ መደናገጡን የሚያመለክት ለመሆኑ ኢማኑዌል ቁልጭ አድርጎ ይተነትናል። በቴክኖሎጂ መበልጸግና የአቶም ኃይልን ማሳደግ ለሱ ብቻ ተባርኮ የተሰጠ በማስመሰል በተለያየ መንገዶች የእነዚህን አገሮች መዳከምና መውደቅ ያዘጋጃል። አሜሪካን ዛሬ ብቸኛነቱን በመምረጥና በመፍራት እራሱ የተስማማባቸውን ዐለም አቀፋዊ ህጎች በመጣስና አዲስ በሚመሰረቱ ኢንስቲቱሽኖች ውስጥ አልገባም በማለት ወይም ደግሞ ስምምነቶችን አልፈርምም በማለት ከአልሚነት ወደአፍራሽነት የሚጓዝ አደገኛ ኃይል ነው። በንጹህ የሚሊታሪና የበላይነት ሎጂክ በማሰብና በመወጠር እንዲሁም ደግሞ በተለያዩ አገሮች ውስጥ ጣልቃ በመግባትና የከፋፍለህ ግዛ ፖሊሰ እንዲሰፍን በማድረግ የዐለምን ሰላም የሚያደፈርስ ፣ በዚህ ጫወታ ብቻም ማንነቱን ለማቆየት የተገነዘበ ኃይል ነው።ይህም የውድቀቱ ዐይነተኛ ምልክት ነው።

ኢማኑዌል ቶድ እንደሚያሳስበን በተለይም እንደ አውሮፓ የመሰሉ የተሻለ ታሪክና የህ ብረተሰብ አወቃቀር ያላቸው የአሜሪካንን የህብረተሰብ ሞዴል እንዳይከተሉ አጥብቆ

ያሳስባል። ኢማኑዔል እንደሚለው የአውሮፓው ህብረተሰብ ከሞላ ጎደል በስምምነትና በመተሳሰብ ላይ የተገነባ ሲሆን መንግሰት በተለያዩ የሙያም ሆነ የአምራች ድርጅቶች ዘንድ ግጭቶች እንዳይፈጠሩ ጣልቃ በመግባት የህብረተሰቡን አረማመድ የሚያግዝ ሚዛናዊ ኃይል ነው።ስለዚህ ይህንን የተፈተነ መንገድ ጥሎ የአሜሪካኖችን መንገድ መከተል ቀስ በቀስ ህብረተሰብአዊ ግጭት እንዲፈጠር መንገዱን ማዘጋጀት ነው ብሎ ያሳስባል።

በአጠቃላይ የኢማኑዔልን መጽሀፍ ለአነበበ የራሱ የሆነ አሰራር ስልትና የቲዎሪ መመረያ እንዳለው መገንዘብ ይቻላል። የኒዎ-ሊበራል ቲዎሪን አቀራረብና መመሪያ እን ደሚቃወም ከአተናተኑ መረዳት ይቻላል። ይሁንና ግን ፣ በተለይም የነፃ ንግድንና የሊበራል ኢኮኖሚን ለመቃወም የሚነሳበት መንደርደሪያ የተሟላ አይደለም። ለምሳሌ ከታሪክ አንፃር የዛሬው የኒዎ ሊበራል ሞዴል እንዴት እንደዳበረ በጥልቅ ቢመረምር ኑሮ ለጽሁፉ ከፍተኛ ጥራት በሰጠው ነበር። ሁለተኛ ፣ ዛሬ ሶስተኛ ዓለም ተብለው የሚጠሩት አገሮች ውስጥ የተስፋፋው ትምህርትና ንቃተ-ህሊና የቱን ያህል በ17ኛውና በ18ኛው ክፍለ ዘመን አውሮፓ ውሰጥ ከተስፋፋው የምሁር እንቅስቃሴ (Enlightenment) ጋር እንደሚመሳሰል ግልጽ አይደለም። እስከገባኝ ድረስ የአውሮፓው የምሁር እንቅስቃሴ በብዙ እጅ ጥራት አለው።ዓለማውም የታወቀ ነበር። ዛሬ በሶስተኛው ዓለም አገሮች የምናየው ትምህርት አጅግ የተዘበራረቀና ዓላማውም በግልጽ የታወቀ አይደለም። ከዚህ ባሸገር መጻፍና ማንበብ በመስፋፋቱ ግለሰብአዊነት ሊዳብር ችሏል የሚለው አገላለጽ ፣ ግለሰብአዊነት ከከፍተኛ ን ቃተ-ህሊናና ከህብረተሰብአዊ ኃለፊነት ጋር የቱን ያህል ተያይዞ መሄድ እንደቻለ ኢማኑዔል ግልጽ አላደረገም። ከዚህም ስንነሳ የኢማኑዔል ግለሰብአዊነት ትርጉም በሆበስአዊ(Hobbes) ላይ የተመረኮዘ የራስን ጥቅም ብቻ ማሳዳድና(Utilitarian Concept) በፕላቶናዊ የማሰብ ኃይልን በማሳደግ ፈጣሪ መሆንና ህብረተሰብአዊ ኃላፊነትን መቀበል( a self-contained individual or a monad) ያለውን ልዩነት በቲዎሪና በፍልስፍና በመመርኮዝ ግልጽ ትንተና አላቀረበም። እንደዚሁም በአሜሪካን የህብረተሰብ አመሰራረት ታሪክ ውስጥ ሁለት አቅጣጫዎች እንደነበሩና የዛሬው የኦሊጋርኪ ሞዴል የመጀመሪያውን ከሞላ ጎደል እየተጋፋውና በአሸናፊነት እንደወጣ ማስታወስ ይቻላል። የአሜሪካንን ህገ-መንግስት ለተመለከተ ፣ የእነ አብርሃም ሊነከንንን የፖለቲካ ፍልስፍና ላጠና የመጀመረያ የህብረተሰብ ውጥን የዛሬው ዐይነቱን እንደሚቀናቀን መገንዘብ ይቻላል። ከዚህ ጋር በሚገባ መታየት ያለበት የዛሬው የአሜሪካ የመንግስት መኪና ፋሽሽታዊ እየሆነ በመሄድና የሚሊታሪውና የስለላ መሳሪያው ሚና እየጎላ እንደ መጣ ኢማኑዔል የአንድ መንግሰት ሚና ከተፈጥሮ ህግ አንፃር ምን መምሰል እንዳለበት በጥብቅ ለመመርመር አይቃጣም። ያም ሆነ ይህ የኢማኑዔል መጽሀፍ መነበብ ያለበት ፣ እንደነ ሀንቲግትና ብሪዚኔብስኪ መጽሀፍ ሳይሆን በን ጹህ ጭንቅላት እጅግ ግሩም በሆነ መልክ የተደረሰ መጽሀፍ ነው። ብዙ ትምህርቶችን ያቀፈና ለምርምር የሚረዳ ፣ በተለይም ደግሞ በህብረተሰብ ግንባታ ውስጥ እንካፈላለን ለሚሉ ኃይሎች የዓለምን የፖለቲካና የኢኮኖሚ አረማመድ ሁኔታ ለመገምገም መንደርደሪያ ለሆን የሚችል በጣም ጥሩ መጽሀፍ ነው። መጽሀፉ በተለያዩ ቋንቋዎች የተተረጎመ ስለሆነ ገዝቶ ማንበብ ይቻላል።

<u>የመጽሀፉ አርዕስት</u> ፣ **Super Power America: Posthumous**

**ፈቃዱ በቀለ / በርሊን**